የገንዘብ ሚኒስቴር
MINISTRY OF FINANCE

# መመሪያ ቁጥር 1064/2017
# የኢንቨስትመንት ማበረታቻን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ

# DIRECTIVE NO. 1064/2025

# A DIRECTIVE ISSUED TO IMPLEMENT INVESTMENT INCENTIVES

ግንቦት፣ 2017 ዓ.ም
May, 2025



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

## መመሪያ ቁጥር 1064/2017
## የኢንቨስትመንት ማበረታቻን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ የገንዘብ ሚኒስቴር ለደንቡ አፈጻጸም የሚያግዙ መመሪያዎችን እንዲያወጣ የሚደነግግ በመሆኑ፤

ኢንቨስተሮች ማበረታቻ የሚያገኙበትን ሁኔታን፣ በደንቡ በተደነገገው መሰረት ግዴታቸውን ያልተወጡ ኢንቨስተሮች የሚኖርባቸውን ተጠያቂነት እና በታክስ እፎይታ ምክንያት የታጣውን የመንግስት ገቢ በትክክል ለማወቅ የሚያስችል የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ (እንደተሻሻለው) ቁጥር 517/2014 አንቀጽ 26 እና የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 19(4) በተሰጠው ስልጣን መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል።

## DIRECTIVE NO. 1064/2025
## DIRECTIVE ISSUED FOR THE IMPLEMENTATION OF INVESTMENT INCENTIVES

Whereas the Investment Incentives Regulation issued by the Council of Ministers provides that the Ministry of Finance shall issue directives to facilitate the implementation of the Regulation;

Whereas it has become necessary to establish a reporting system that accurately identifies the conditions under which investors are granted incentives, determines the liabilities of investors who fail to fulfill their obligations as stipulated by the Regulation, and assesses the government revenue forgone due to tax holidays;

NOW, THEREFORE, in accordance with the authority vested in it under Article 26 of the Investment Regulation No. 517/2022 (as amended) and Artcile 19(4) of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs Proclamation No. 1263/2021, the Ministry of Finance hereby issues this Directive.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**የኢንቨስትመንት ማበረታቻን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 1064/2017**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1. "**የገቢ ግብር እፎይታ**" ማለት ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ግብር በሚከፈልበት ገቢው ላይ ሊከፍል የሚገባውን ግብር ሙሉ በሙሉ እንዳይከፍል የሚሰጥ ችሮታ ነው፡፡
2. "**ሚኒስቴር**" ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፡፡
3. "**የታክስ ባለስልጣን**" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ነው፡፡
4. "**ደንብ**" ማለት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (እንደተሻሻለው) ቁጥር 517/2014 ነው፡፡
5. በኢንቨስትመንት ደንብ ትርጉም የተሰጣቸው እና በዚህ መመሪያ ያልተተረጎሙ ቃላት እና ሐረጎች በደንቡ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

## SECTION ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Directive may be cited as the **"Directive for the Implementation of Investment Incentives No. 1064/2025."**

### 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Directive:

1. **"Income Tax Holiday"** means an incentive that fully exempts a taxpayer, who is otherwise liable to pay income tax on taxable income, from the payment of such tax;
2. "**Ministry**" means the Ministry of Finance;
3. "**Tax Authority**" means the Ministry of Revenues;
4. "**Regulation**" means the Council of Ministers Investment Incentives Regulation No. 517/2022 (as amended);
5. Words and phrases defined in the Regulation but not specifically defined in this Directive shall have the meanings assigned to them in the Regulation.

## ክፍል ሁለት
## የገቢ ግብር እፎይታ

### 3. የገቢ ግብር እፎይታ ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

## SECTION TWO
## INCOME TAX HOLIDAY

### 3. Conditions for Being a Beneficiary of Income Tax Holiday



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

1. ማናቸውም ኢንቨስተር በደንቡ የተመለከተው የግብር እፎይታ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው፤
   ሀ) ማበረታቻ በተፈቀደለት የኢንቨስትመንት መስክ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲያቀርብ፤
   ለ) አግባብ ባለው የመንግሥት አካል የተሰጠ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሲያቀርብ፣ እና
   ሐ/ አግባብ ባለው የፌዴራል ወይም የክልል የኢንቨስትመንት ባለስልጣን ኢንቨስትመንቱን ማጠናቀቁን የሚያረጋግጥ እና የታክስ እፎይታ እንዲሰጠው የሚጠይቅ የድጋፍ ደብዳቤ ሲያቀርብ፤ ይሆናል፡፡
2. የኢንቨስትመንት ማሻሻያ ወይም ማስፋፊያን በሚመለከት ለኢንቨስትመንት ማስፋፊያ/ ማሻሻያ ስለሚሰጥ ማበረታቻ አፈጻጸም የወጣው መመሪያ ቁጥር 941/2015 የተደነገጉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ይሆናል፡፡

1. Any investor may benefit from the income tax holiday provided under the Regulation if the following conditions are fulfilled:
   a) The investor submits an investment license in an investment field that is eligible for incentives;
   b) The investor submits a business license issued by the appropriate government body;
   c) The investor submits a letter of support from the appropriate federal or regional investment authority confirming the completion of the investment and requesting the grant of income tax holiday.
2. The implementation of the incentive for investment expansion or upgrading shall be subject to the fulfillment of the conditions stipulated under Directive No. 941/2023 therein.

## 4. የሂሳብ መግለጫን ዘግይተው በሚያቀርቡ ላይ ስለሚጣል ቅጣት

1. የግብር እፎይታ የተሰጠው ኢንቨስተር በታክስ እፎይታው ጊዜ ውስጥ ሊያቀርብ የሚገባውን የሂሳብ መግለጫ በገቢ ግብር አዋጅ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ለታክሱ ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡
2. ኢንቨስተሩ የሂሳብ መግለጫውን በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ከተመለከተው ጊዜ ዘግይቶ ካቀረበ በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተመለከተውን አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፡፡

## 4. Penalties for Late Submission of Financial Statements

1. An investor granted a tax holiday must submit to the Tax Authority the financial statements required under the Income Tax Proclamation within the period specified therein.
2. If the investor submits the financial statements beyond the period specified under Sub-Article 1 of this Article, the investor shall be subject to the administrative penalty prescribed under the Tax Administration Proclamation.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

## 5. ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ገቢን ያለማስታወቅ

በደንቡ አንቀጽ 8(4) በተደነገገው መሰረት ገቢውን የማስታወቅ ግዴታውን ያልተወጣ ባለሃብት ገቢውን ያላስታወቀው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት እንደሆነ ተቆጥሮ ከቅጣት እና ወለድ ነጻ እንዲሆን ወይም በግብር እፎይታው መጠቀሙን እንዲቀጥል ለመፍቀድ የሚቻለው ባለሃብቱ ግዴታውን ያልተወጣው የኢንቨትመንት ስራውን በሚያከናውንበት ቦታ በተፈጠረ ሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ወይም በጦርነት ምክንያት ሂሳቡን ዘግቶ ገቢውን ማስታወቅ ያልቻለ መሆኑ አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት ባለስልጣን ሲረጋገጥ ነው።

## 5. Failure to Declare Income Due to Force Majeure

An investor who fails to declare income may be considered to have failed to do so due to force majeure and may be exempted from penalties and interest or allowed to continue benefiting from the tax holiday in accordance to Article 8(4) of the Regulation, if it is proven that the investor, due to a man-made or natural disaster or war in the area where the investment activities are carried out, has closed accounts and was unable to declare income.

## 6. የግብር እፎይታን ስለመሰረዝ

በደንቡ መሰረት የተሰጠ የግብር እፎይታ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሰረዝ ይችላል፦

ሀ) የግብር እፎይታው የተፈቀደው በሃሰት ወይም በተጭበረበረ መረጃ ወይም ሰነድ ላይ ተመስርቶ ከሆነ፤

ለ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠበት የኢንቨስትመንት ተግባር መቋረጡ ከተረጋገጠ፤

ሐ) ኢንቨስተሩ በደንቡ በተመለከተው መሰረት ለታክሱ ባለስልጣን የተሟላ የሂሳብ መግለጫ ያላቀረበ ወይም ሌሎች በደንቡ የተመለከቱ ግዴታዎቹን ያልተወጣ ከሆነ፤

## 6. Cancellation of Tax Holiday

A tax holiday granted under the Regulation may be revoked for the following reasons:

a) If the tax holiday was granted based on false or fraudulent information or documents;

b) If it is confirmed that the investment activity for which the investment license was granted has been terminated;

c) If the investor has failed to submit a complete financial statement to the Tax Authority or has not fulfilled other obligations as required by the Regulation.

## 7. የግብር እፎይታ ከመሰረዙ በፊት መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች

1. በደንቡ በተደነገገው መሰረት የግብር እፎይታ የሚሰረዘው በሚኒስቴሩ ነው።

2. የግብር እፎይታን የመሰረዝ እርምጃ አፈጻጸም የሚከተለውን ስርአት መከተል አለበት፦

## 7. Steps to be taken before Tax Holiday Is Revoked

1. Tax exemptions shall be revoked by the Ministry as prescribed under the Regulation.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

ሀ) የሚመለከተው የታክስ ወይም የኢንቨስትመንት ባልስልጣን ለኢንቨስተሩ የተሰጠው የገቢ ግብር እፎይታ ሊሰረዝ እንደሚገባ ሲያምን ይህንኑ ለሚኒስቴሩ በጽሁፍ ያስታውቃል።

ለ) ሚኒስቴሩ የገቢ ግብር እፎይታ እንዲሰረዝ ጥያቄ ለቀረበበት ኢንቨስተር ለገቢ ግብር እፎይታው መሰረዝ ምክንያቱን በመጥቀስ በጉዳዩ ላይ በ10 ቀናት ጊዜ ውስጥ ማብራሪያ እንዲሰጥ ይጠይቃል።

ሐ) ኢንቨስተሩ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ ወይም የሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ሚኒስቴሩ የገቢ ግብር እፎይታው እንዲሰረዝ ውሳኔ ይሰጣል፤ ይህንኑም ለኢንቨስተሩ ያስታውቃል።

3. የገቢ ግብር እፎይታው የተሰረዘበት ኢንቨስተር ውሳኔው በተገለጸለት በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በደንቡ በተመለከተው መሰረት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።

2. The implementation of the cancellation of the tax holiday shall follow the procedure outlined below:
   a) When the relevant tax or investment authority believes that the income tax relief granted to the investor should be revoked, it shall notify the Ministry in writing.
   b) The Ministry shall request the investor, against whom a request for cancellation of the income tax relief has been made, to submit an explanation within 10 days, stating the reasons for the cancellation of the tax holiday.
   c) If the investor does not respond within the given period or if the response is deemed unsatisfactory, the Ministry shall decide to cancel the income tax holiday and notify the investor accordingly.
3. An investor whose income tax holiday has been revoked may file an appeal within 30 days of receiving notification of the decision, as stipulated in the Regulation.

## 8. የግብር እፎይታ መሰረዝ የሚያስከትለው ውጤት

የግብር እፎይታ የተሰረዘበት ኢንቨስተር በግብር እፎይታው ምክንያት ሳይከፍል የቀየውን ግብር ከነወለዱ እና መቀጫው እንዲከፍል ይደረጋል።

## 8. Consequences of the Revocation of Tax Holiday

An investor whose tax holiday has been revoked shall be required to pay the taxes that were previously exempted, along with any applicable interest and penalties.

## 9. የግብር እፎይታን በሚመለከት በታክሱ ባለስልጣን የሚያዝ መረጃ

## 9. Information Required by the Tax Authority Regarding Tax Holiday

1) The Tax Authority must maintain the following information regarding



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

1. የታክሱ ባለስልጣን የግብር እፎይታ የተሰጣቸውን ኢንቨስተሮች በሚመለከት የሚከተለውን መረጃ መያዝ አለበት፦
   ሀ) የኢንቨስተሩን ስም እና አድራሻ፣
   ለ) የተሰማራበትን የኢንቨስትመንት መስክ፣
   ሐ) የተሰጠውን የግብር እፎይታ የጊዜ ርዝመት፤
   መ) የግብር እፎይታው ለአዲስ ወይም ለማስፋፊያ/ማሻሻያ ኢንቨስትመንት የተሰጠ መሆኑን፣
   ሠ/ ለግብር እፎይታው መሰረት የሆነውን የህግ ድንጋጌ፣ እና
   ረ) በግብር እፎይታው ምክንያት የታጣው ገቢ፡፡
2. የታክሱ ባለስልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የያዘውን መረጃ ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ በየሶስት ወሩ ወር በገባ እስከ አስራ አምስተኛው ቀን ለሚኒስቴሩ መላክ አለበት፡፡

**10.ለልዩ የኢኮኖሚ ዞን የሚሰጥ የገቢ ግብር እፎይታ**

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እውቅና የተሰጠው ልዩ የኢኮኖሚ ዞን አልሚ፤ የልዩ ኤኮኖሚ ዞን ንኡስ አልሚ፤ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ እና የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ድርጅት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ለተመለከተው ጊዜ ያህል የገቢ ግብር እፎይታ ያገኛሉ፡፡

investors who have been granted a tax holiday:

a) The investor's name and address;
b) The investment field in which the investor is engaged;
c) Whether the tax relief is granted for a new investment or for an expansion/upgrading investment;
d) The legal provision serving as the basis for the tax relief;
e) The duration of the tax holiday granted;
f) The amount of revenue forgone due to the tax holiday.

4. The Tax Authority shall submit the information obtained pursuant to Sub-Article 1 of this Article to the Ministry by the fifteenth day of the first month of each quarter, commencing on July 1.

**10. Tax Holiday for Special Economic Zones**

A special economic zone developer, special economic zone sub-developer, special economic zone administrator, and special economic zone enterprise operating within a special economic zone recognized by the Ethiopian Investment Board shall be entitled to the tax holiday provided in the schedule attached to this Directive.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

## 11.ሚስማር እና ቆርቆሮ ማምረት

ከደንቡ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ተራ ቁጥር 1.13.1 ለሚስማር እና ቆርቆሮ ማምረት ስራ የገቢ ግብር ነጻ መብት እንደማይፈቀድ የተመለከተው ግብአቶቹን ከማምረት ጀምረው ቆርቆሮ እና ሚስማር ጭምር የሚያመርቱትን አይጨምርም።

## 11. Nails and Iron Sheets

Item number 1.13.1 of the Annex attached to the Regulation, which excludes the manufacturing of nails and iron sheets, does not apply to metal industries that produce nails and iron sheets starting from the raw input stage.

## 12. ኪሳራ በሚሸጋገርበት ዘመን ስለሚያጋጥም ኪሳራ

1. ማንኛውም ባለሃብት በደንቡ አንቀጽ 10 መሰረት በገቢ ግብር እፎይታ ዘመን ኪሳራ ያጋጠመው እንደሆነ ይህ ኪሳራ የግብር እፎይታው ከተጠናቀቀ በኋላ ባለው የእፎይታው ዘመን ግማሽ በሚሆን ጊዜ ከተገኘ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ጋር እንዲካካስ ይደረጋል።
2. ኪሳራው በሚካካስበት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ያጋጠመ ኪሳራ ቢኖር አይካካስም።

## 12. Loss Carry-Forward During the Period of Loss

1. An investor who incurs a loss during the income tax holiday period, pursuant to Article 10 of the Regulation, shall be entitled to offset such loss against taxable income earned during the half incentive period following the end of the tax holiday.
2. Any loss incurred during the period referred to in Sub-Article 1 of this Article, during which loss carry forward has already been provided, shall not be subject to further compensation.

## 13. ለማስፋፊያ የተሰጠ ማበረታቻ አፈጻጸም

1. በደንቡ እና በኢንቨስትመንት ማስፋፊያ/ማሻሻያ መመሪያ ለማስፋፊያ/ለማሻሻያ የገቢ ግብር እፎይታ ለማግኘት የሚያስፈልገውን መስፈርት አሟልቶ የገቢ ግብር እፎይታ የተሰጠው ባለሃብት በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ እና አስተዳደራዊ ምክንያቶች በእፎይታ ዘመኑ የሚያመርተው ምርት መጠን በማስፋፊያ ወቅት ከነበረው ቢቀንስ የገቢ ግብር እፎይታውን ሊያጣ አይችልም።

## 13. Implementation of the Incentive Given for Expansion

1. An investor who has fulfilled the requirements for income tax holiday for expansion or upgrading under the Regulation and the Investment Expansion/Upgrading Directive, and who has been granted income tax holiday, shall not forfeit such relief if the volume of production during the relief period decreases from the volume during the expansion period due to various economic or administrative reasons.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

2. የማስፋፊያ የገቢ ግብር እፎይታ የተሰጠው ባለሃብት ይህንኑ የማስፋፊያ ስራ በሚያከናውንበት ጊዜ ወደአገር ባስገባቸው እቃዎች ላይ የከፈለው የገቢ ግብር የቅድሚያ ክፍያ ቢኖር ተመላሽ ይደረጋል፡፡

## 14. የእህል ምርት ማቀነባበር

1. ከደንቡ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ለእህል ምርት ማቀነባበር የተሰጠው ማበረታቻ ተፈጻሚ የሚሆነው አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የእህል ምርቶችን በመደባለቅ፤ አንድ ላይ በመፍጨት፤ በመቀቀል፤ ባማዋሃድ ወይም በሌላ ኬሚካላዊ ዘዴ አንድ የተለየ ምርት ለማውጣት ተግባር ብቻ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም እንጀራ፣ ዳቦ፣ የባልትና ውጤቶችን እና የመሳሰሉትን የምግብ ውጤቶች ማቀነባበርን አይጨምርም፡፡

## 15. የቴክኒክ እና ሙያ ስልጠና

ከደንቡ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና (ስፖርትን ጨምሮ) የተሰጠው ማበረታቻ የሰውነት ማጎልበቻ እንቅስቃሴ የሚከናወንበትን ጂምናዚየም አይጨምርም፡፡

2. An investor who has been granted an income tax exemption for expansion shall be entitled to a refund of any advance income tax paid on goods imported into the country during the expansion period.

## 14. Processing of Grain Products

1. The incentive granted for the processing of grain products, as stated in the schedule attached to the Regulation, applies to the processes of mixing one or more grain products, grinding, boiling, blending, or using any other chemical method to produce a specific product, excluding mere changes in the shape of the grain.

2. Notwithstanding Sub-Article 1 of this Article, the incentive shall not apply to the processing of enjera, bread, home-prepared foodstuff (baltena products) or similar food products.

## 15. Technical and Vocational Training

The incentive provided for technical and vocational training (including sports), as specified in the table attached to the Regulation, shall not apply to gymnasiums where bodybuilding activities are conducted.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

## ክፍል ሦስት
## ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ የመሆን ማበረታቻ

**16. የግንባታ እቃዎች ከቀረጥ ነፃ ሆነው የሚገቡበት ሁኔታ**

1. በደንቡ መሰረት ባለሀብቶች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር ማስገባት የሚችሉት የግንባታ ዕቃዎች የሚከተሉትን ብቻ ነው፤
   - ሀ/ የግንባታ ብረት፣
   - ለ/ በር እና መስኮት ከእነ አክሰሰሪዎቹ፣
   - ሐ/ መስታወት፣
   - መ/ ስቲል ስትራክቸር፣
   - ሠ/ ሴራሚክ፤ ለትምህርት፣ ሆቴል እና ለሆስፒታል ብቻ፤ እና
   - ረ/ አልሙኒየም፣ ለትምህርት፣ ለሆቴል እና ለሆስፒታል ብቻ፤

2. ወደአገር እንዲገቡ የተፈቀደ የግንባታ እቃዎች ከቀረጥ ነጻ ሆነው ሊገቡ የሚችሉት በሚከተለው ቅደም ተከተል ይሆናል፡-
   - ሀ) ለግንባታ ስራው ማስጀመሪያ የሚውል በግንባታ እቃዎች ብዛት ሰነድ ከተመለከተው የግንባታ እቃዎች ብዛት ውስጥ 30% (ሰላሳ በመቶ)፤
   - ለ) ወደአገር የገባው የግንባታ እቃ ለታለመለት አላማ መዋሉን የግንባታ ስራውን የሚቆጣጠረው የመንግስት አካል በጽሁፍ

## SECTION THREE

## INCENTIVES FOR EXEMPTION FROM CUSTOMS DUTIES

**16. Conditions for Importation of Construction Materials Exempt from Tax**

1. Pursuant to the Regulation, investors may import only the following construction materials into the country free of duty and tax:
   - a. Construction steel;
   - b. Doors and windows, including their accessories;
   - c. Glass;
   - d. Steel structures;
   - e. Ceramic materials, limited to use in educational institutions, hotels, and hospitals;
   - f. Aluminum materials, limited to use in educational institutions, hotels, and hospitals.

2. Construction materials permitted to be imported duty-free shall be imported in the following sequence:
   - a) 30% (thirty percent) of the quantity of construction materials specified in the document may be imported to commence construction work;
   - b) 30% of the remaining 70% of the construction materials may be imported when the government body supervising the construction work certifies in writing that the previously



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

ሲያረጋግጥ በግንባታ እቃዎች ብዛት ሰነድ ከተመለከተው ቀሪው 70% (ሰባ በመቶ) የግንባታ እቃ ውስጥ 30% (ሰላሳ በመቶ)

ሐ) በመጨረሻም ወደአገር የገባው 60% የግንባታ እቃ ለታለመለት አላማ መዋሉን የግንባታ ስራውን የሚቆጣጠረው የመንግስት አካል በጽሁፍ ሲያረጋግጥ በግንባታ እቃዎች ብዛት ሰነድ ከተመለከተው ቀሪው 40% (አርባ በመቶ) ከቀረጥ ነጻ ሆኖ ይገባል፡፡

imported materials have been used for their intended purpose;

c) The remaining 40% (forty percent) of the quantity of construction materials may be imported duty-free once the supervising authority certifies in writing that 60% of the previously imported materials have been used for their intended purpose.

3. ኢንቨስተሩ በተለያዩ ምክንያቶች በግንባታ እቃዎች ብዛት ሰነድ የተመለከቱትን የግንባታ እቃዎች ሙሉ በሙሉ ወይም አብዛኛውን በአንድ ጊዜ ለማስገባት የሚፈልግ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንኡስ 2 ያለማረጋገጫ ወደአገር እንዲያስገባ ከተፈቀደለት በላይ ያለው መጠን ለታለመለት አላማ የሚውል ለመሆኑ ዋስትና እንዲሆን በቀረጥ እና ታክሱ ልክ በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሰረት የባንክ ወይም የጥሬ ገንዘብ ዋስትና ለጉምሩክ ኮሚሽን ማቅረብ አለበት፡፡

4. ኢንቨስትሩ በዚህ አንቀጽ መሰረት በየደረጃው ወደአገር ያስገባው መጠን በአንቀጹ ከተፈቀደው ያነሰ ከሆነ የግንባታ ስራውን ከሚቆጣጠረው የመንግስት አካል የአፈጻጸም ሪፖርት እንዲያቀርብ የሚገደደው ወደአገር ላስገባው መጠን ብቻ ይሆናል፡፡

5. የጉምሩክ ኮሚሽን በደንቡ አንቀጽ 17 መሰረት የግንባታ እቃዎችን ጨምሮ ከቀረጥ ነጻ ሆነው ወደአገር በገቡ እቃዎች ላይ የድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት ማድረግ አለበት፡፡

3. If the investor, for any reason, wishes to import all or a substantial portion of the construction materials specified in the construction materials quantity document at once, the investor shall be required to provide a bank or cash guarantee to the Customs Commission in accordance with the provisions of the Customs Proclamation which serve as assurance that the quantity exceeding the amount permitted to be imported without verification under Sub-Article 2 of this Article will be used solely for its intended purpose,.

4. If the quantity of materials imported at each stage is less than the quantity permitted under this Article, the government body supervising the construction work shall submit a performance report for the quantity actually imported.

5. The Customs Commission, pursuant to Article 17 of the Regulation, must conduct a customs clearance audit on goods imported duty-free, including construction materials.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

## 17. ለካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ስለሚሰጥ የጉምሩክ ማበረታቻ

ለካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ሥራ ላይ የተሰማራ ባለሀብት ወደ አገር የሚያስገባቸው የካፒታል ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ ሊሆኑ የሚችሉት የካፒታል ዕቃው ጥቅም ላይ የሚውልበት ዘርፍ በደንቡ እና በዚህ መመሪያ ጋር በተያያዙት ሰንጠረዦች የካፒታል ዕቃ ማበረታቻ የተፈቀደለት ሲሆን ነው፡፡

## 18. እቃዎችን ከአገር ውስጥ ስለመግዛት

1. በደንቡ እና በዚህ መመሪያ የካፒታል እቃዎችን፣ የግንባታ ዕቃዎችን፣ መለዋወጫዎችን እና ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገቡ የተፈቀደላቸው ባለሃብቶች በብዛት፤ በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገኝ እስከሆነ ድረስ ከቀረጥ ነጻ ሆነው ወደአገር እንዲገቡ የተፈቀደ እቃዎችን ግዢ ከአገር ውስጥ መፈጸም አለባቸው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን መስፈርት በሚያሟላ አኳኋን ዕቃው በአገር ውስጥ የሚገኝ መሆኑ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከተረጋገጠ ሚኒስቴሩ የጉምሩክ ቀረጥ ማበረታቻን መፍቀድ የለበትም፡፡
3. ባለሃብቶች በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ከአገር ውስጥ ግዢ በሚፈጽመበት ጊዜ እቃውን ለማምረት በዋለ ግብአት ላይ የተከፈለ ማናቸውም ቀረጥ እና ታክስ በጉምሩክ ኮሚሽን አማካኝነት ተመላሽ ይደረጋል፡፡

## 17. Customs Incentives for Leasing Capital Goods

An investor engaged in the leasing of capital goods may import such goods duty-free if the sector in which the capital goods are used is eligible for capital goods incentives in accordance with the Regulation and the tables attached to this Directive.

## 18. Purchasing Goods Domestically

1. Investors permitted to import capital goods duty-free under the Regulation and this Directive must purchase such goods domestically if they are available in sufficient quantity, of appropriate quality, and at a reasonable price.
2. If the Ministry of Industry confirms that goods meeting the criteria specified under Sub-Article 1 of this Article are available domestically, the Ministry shall not give customs duty incentives for the importation of such goods.
3. When investors purchase goods domestically in accordance with Sub-Article 1 of this Article, any duties and taxes paid on the inputs used to produce these goods shall be refunded by the Customs Commission.
4. For purposes of implementing this Article, the Ministry of Industry shall



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

4. በዚህ አንቀጽ መሰረት የጉምሩክ ኮሚሽን የተመላሹን ክፍያ መፈጸም እንዲችል የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የግብአት ምርት ጥመርታ አዘጋጅቶ ይሰጣል።

prepare input-output coefficients to enable the Customs Commission to process refunds accordingly.

## 19. የካፒታል እቃዎች ዝርዝር

1. በደንቡ ሰንጠረዥ እና ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ዝርዝር ውስጥ በተካተቱ ዘርፎች የሚሰማሩ ባለሃብቶች ከቀረጥ ነጻ ሆነው ወደአገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ከአገር ውስጥ ለመግዛት የሚችሉት ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው አባሪ 2 የተመለከቱትን የካፒታል እቃዎች ብቻ ነው።

2. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተጠቀሰው አባሪ የተመለከቱትን የካፒታል እቃዎች ዝርዝር ሊያሻሽል ይችላል።

## 19. List of Capital Goods

1. Investors engaged in sectors listed in the Schedule of the Regulation and the list annexed to this Directive may import or purchase domestically, tax-free, only the capital goods listed in Annex 2 attached to this Directive.

2. The Ministry may amend the list of capital goods referred to in the Annex under Sub-Article 1 of this Article.

# ክፍል አራት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 20. በተሻሩ ህጎች የተሰጡ ማበረታቻዎች ቀጣይነት

1. በደንቡ አንቀጽ 27 (2) በተደነገገው መሰረት የተሻረው የኢንቨስትመንት ማበረታቻ እና ለሃገር ውስጥ ባለሃብቶች የተከለሉ የስራ መስኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/ 2005 (እንደተሻሻለው) መሰረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጡ እና ማበረታቻ የተሰጣቸው ባለሃብቶች በተሻረው ደንብ የተሰጣቸውን ማበረታቻ ያገኛሉ።

# SECTION FOUR

# MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 20. Continuation of Incentives Provided Under Repealed Laws

1. Investors who have been issued an investment license and received incentives pursuant to the repealed Investment Incentives and Areas of Operation Reserved for Domestic Investors Regulation No. 270/2005 (as amended) shall, in accordance with Article 27(2) of the Regulation, continue to receive the incentives provided under the repealed Regulation.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

2. በማዕድን እና የነዳጅ ስራዎች አዋጅ መሰረት ማበረታቻ ተሰጥቷቸው የነበረ በማእድን እና በነዳጅ ስራዎች የተሰማሩ ባለሃብቶች የተሰጣቸው ማበረታቻ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡
3. ማናቸውም ኢንቨስተር ደንቡ ከመውጣቱ በፊት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም የኢንቨስትመንት ማሻሻያ/ማስፋፊያ ፈቃድ የወሰደ ቢሆንም አዲሱ ደንብ የተሻለ የታክስ ማበረታቻ የሚያስገኝለት ከሆነ በደንቡ መሰረት ማበረታቻውን ሊያገኝ ይችላል፡፡
4. ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጡ ባለሃብቶች በደንቡ እና ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ተፈፃሚነት በነበራቸው መመሪያዎች መሰረት የተሰጡ ማበረታቻዎችን ያገኛሉ፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገገው የሙከራ ጥሬ ዕቃዎች፣ ከንግድ ሥራ ፈቃድ በኋላ የሚፈቀዱ የግንባታ እና የካፒታል ዕቃዎች፣ ያለ ገደብ የተፈቀዱ የመለዋወጫ፣ የሙከራ ጥሬ ዕቃ፣ የግንባታ እና የካፒታል ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

## 21.በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጸደቁ የማእድን እና የነዳጅ ስምምነቶች

በማዕድን እና የነዳጅ ስራዎች አዋጅ መሰረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በጸደቀ የማእድን እና የነዳጅ ስራዎች ስምምነት የተሰጡ ማበረታቻዎች ተፈጻሚነት ይቀጥላል፡፡

2. Incentives granted to investors engaged in mining and petroleum activities under the Mining and Petroleum Operations Proclamation shall continue to apply.
3. Any investor who obtained an investment license or investment expansion/upgrading license before the issuance of the new Regulation may benefit from the incentives under the new Regulation if it provides better tax incentives.
4. Investors who obtained an investment license prior to the issuance of this Directive shall continue to benefit from the incentives granted under the regulations and directives that were in effect at the time the license was issued.
5. The provision under Sub-Article 4 of this Article shall not apply to commissioning raw materials, construction materials, capital goods permitted after the issuance of a business license, or to unlimited quantities of permitted spare parts, commissioning raw materials, construction materials, and capital goods.

## 21. Mining and Petroleum Agreements Approved by the Council of Ministers

In accordance with the Mining and Petroleum Operations Proclamation, incentives provided under Mining and Petroleum Operations Agreements approved by the Council of Ministers shall continue to apply.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

22.ሰነዶችን ስለማቅረብ

በደንቡ እና በዚህ መመሪያ መሰረት የገቢ ግብር እፎይታ እና የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን ስልጣን ላለው የኢንቨስትመንት አካል የሚቀርቡ ጥያቄዎች በዚህ መመሪያ አባሪ 3 እና አባሪ 4 የተጠቀሱትን ሰነዶች በማሟላት መቅረብ አለባቸው፡፡

23.ሰነድ ያለመሟላት

1. ባለሃብቱ የካፒታል እቃዎች ከቀረጥ ነጻ ሆኖ ወደአገር ለማስገባት የሚያስችሉትን ሰነዶች በደንቡ እና በመመሪያው በተመለከተው መሰረት አሟልቶ ያላቀረበ እና በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለማቅረብ ግዴታ የሚገባ ከሆነ የኢንቨትመንት መስሪያ ቤቱ ይህንኑ በመግለጽ ጥያቄውን ለሚኒስቴሩ ያስተላልፋል፡፡

2. ሚኒስቴሩ የቀረበው ጥያቄ አሳማኝ ሆኖ ካገኘው ባለሃብቱ በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሰረት በዋስትና እንዲስተናገድ ለጉምሩክ ኮሚሽን ሊያስተላለፍ ይችላል፡፡

24.ያለአግባብብ የተወሰዱ የጉምሩክ ቀረጥ ማበረታቻዎች ተመላሽ የሚደረጉበት ሁኔታ

1. ባለሃብቱ የገቢ ግብር እፎይታ እና/ወይም የጉምሩክ ቀረጥ ማበረታቻ ያገኘው በተሳሳተ ወይም በተጭበረበረ መረጃ ላይ በመመስረት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ተቆጣጣሪው ባላስልጣን ወይም የታክሱ ባለስልጣን ይህንኑ ባወቀ በ5 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡
2. ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በቀረበለት ሪፖርት ላይ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**22. Submission of Documents**

Applications submitted to the authorized investment entity for income tax relief and customs duty exemption incentives, in accordance with the Regulation and this Directive, shall be accompanied by the documents listed under Annex 3 and Annex 4 of this Directive.

**23. Incompleteness of Documents**

1. Where an investor fails to submit the documents required for the duty-free importation of capital goods within the prescribed period but if undertakes to submit with in a limited period of time, the Investment Office shall forward the matter to the Ministry, providing appropriate justification.
2. If the Ministry finds the request credible, the investor may proceed to submit the necessary documentation to the Customs Commission under a guarantee, as prescribed by the Customs Proclamation.

**24. Return of Improperly Taken Incentives**

1. Where it is determined that an investor has obtained income tax relief or duty-free privilege based on incorrect or fraudulent information, the supervising authority or the tax authority shall report the matter to the Ministry within five (5) days of becoming aware of the issue.
2. The Ministry shall issue a decision on the report submitted under Sub-Article 1 of this Article within one (1) month.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

## 25.የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች

1. የታክስ እፎይታ እና የቀረጥ ነፃ ማበረታቻን በሚመለከት በተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች እና በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ የወጡ መመሪያዎች እና ውሳኔዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡
2. በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ሌሎች መመሪያዎች፣ ሰነዶች እና አሰራሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## 25. Repealed and Inapplicable Directives

1. All directives and decisions issued by regulatory agencies and the Ethiopian Investment Board concerning tax holidays and customs exemption incentives are hereby repealed.
2. Any directives, documents, or procedures inconsistent with the provisions of this Directive are hereby repealed.

## 26.ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት 18 ቀን 2017 ዓ.ም

አህመድ ሺዴ

የገንዘብ ሚኒስትር

## 25. Effective Date

This Directive shall enter into force as of the date of its registration by the Ministry of Justice and its uploading on the official website of the Ministry of Finance.

Done at Addis Ababa, on the 26th May of 2017.

Ahmed Shide
Minister of Finance



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

## አባሪ አንድ
## የገቢ ግብር እፎይታ እና/ወይም ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ የመሆን መብት የተሰጣቸው የኢንቨስትመንት መስኮች

| ተራ ቁጥር | የኢንቨስትመንት መስክ | የገቢ ግብር እፎይታ | |
|---|---|---|---|
| 1 | **ልዩ የኢኮኖሚ ዞን** | **በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን** | **በሌሎች አካባቢዎች** |
| 1.1. | የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አልሚ | ለ 10 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 15 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.2. | የልዩ ኤኮኖሚ ዞን ንኡስ አልሚ | ለ 7ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 10 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.3. | የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አስተዳዳሪ | ለ 5 ዓመት ከገቢ ብር ነፃ የመሆን | ለ 7 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 1.4. | የልዩ ኤኮኖሚ ዞን ድርጅት | ለ 5 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን | ለ 7 ዓመት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን |
| 2 | **የማኑፋቸሪንግ ኢንዱስትሪ** | | |
| 2.1. | ማሽጊያ እና ሌብሊንግ ማምረት | አያገኝም | አያገኝም |
| 2.2. | ሰንደል ማምረት | አያገኝም | አያገኝም |
| 2.3. | አውሮፕላን ማምረት | 6 ዓመት | 7 ዓመት |
| 2.4. | የአውሮፕላን አካላት ማምረት | 4 ዓመት | 5 ዓመት |
| 2.5. | ድሮን እና የእነዚህን አካላት ማምረት | አያገኝም | አያገኝም |
| 2.6. | የፈርነስ ዘይት ማምረት | አያገኝም | አያገኝም |
| 3. | የግብርና ዘርፍ | | |
| 3.1. | ችግኝ ማባዛት እና ማምረትን ጨምሮ ቲሹ ካልቸር እና የዘር ማባዛት | አያገኝም | አያገኝም |
| 3.2. | 4.2 ቡና ማጠብ፤ መቀሸር፤ ለኤክስፖርት ማዘጋጀት፤ እና መቁላት | አያገኝም | አያገኝም |



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3.3. | 4.3 የተፈጥሮ ማር / ሰም ማቀነባበር/ ማምረት | አያገኝም | አያገኝም፣ |
| 4 | **አገልግሎት** | | |
| 4.1. | በአውሮፕላን ጸረ ተባይ መርጨት | አያገኝም | አያገኝም |
| 4.2. | በአነስተኛ አውሮፕላን የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት | አያገኝም | አያገኝም |
| 4.3. | የፈሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ እና ማሰወገጃ አገልግሎት | አያገኝም | አያገኝም |
| 4.4. | የውሃ ላይ ጨዋታ እና የማዝናናት አገልግሎት | አያገኝም | አያገኝም |
| 4.5. | ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት | አያገኝም | አያገኝም |
| 4.6. | ክሪፕቶ ከረንሲ ማይኒንግ | አያገኝም | አያገኝም |

**ANNEX ONE**

**INVESTMENT SECTORS ELIGIBLE FOR INCOME TAX INCENTIVES AND/OR CUSTOMS DUTY EXEMPTION**

| Item number | Investment Area | Income Tax Incentive | |
|---|---|---|---|
| | | Addis Ababa and surroundings of Addis Ababa City | Other Areas |
| **1** | **Special economic zone** | | |
| 1.1. | Special Economic Zone Developer | Exemption from income tax for 10 years | Exemption from income tax for 15 years |
| 1.2. | Special Economic Zone Sub-Development | Exemption from income tax for 7 years | Exemption from income tax for 10 years |
| 1.3. | Special Economic Zone Administrator | Exemption from income tax for 5 years | Exemption from income tax for 7 years |
| 1.4. | Enterprises of Special Economic Zone | Exemption from income tax for 5 years | Exemption from income tax for 7 years |



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

| | | | |
|---|---|---|---|
| **2** | **Manufacturing industry** | **No income tax exemption** | **No income tax exemption** |
| 2.1. | Manufacturing of packaging and labeling | No income tax exemption | No income tax exemption |
| 2.2. | Joss-stick (Sandal) manufacturing | No income tax exemption | No income tax exemption |
| 2.3. | Manufacturing of aaircraft and any part thereof. | No income tax exemption | No income tax exemption |
| 2.4. | Manufacturing of drones and any part thereof. | No income tax exemption | No income tax exemption |
| 2.5. | Production of Furnace oil | No income tax exemption | No income tax exemption |
| **3** | **Agricultural sector** | **No income tax exemption** | **No income tax exemption** |
| 3.1. | Seed propagation and production including seedling propagation and Tissue culture | No income tax exemption | No income tax exemption |
| 3.2. | Washing Coffee; grinding( hatching); roasting and preparing for export | No income tax exemption | No income tax exemption |
| 3.3. | Natural honey/wax processing/production | No income tax exemption | No income tax exemption |
| **4** | **Services** | **No income tax exemption** | **No income tax exemption** |
| 4.1. | Spraying pesticides by plane | No income tax exemption | No income tax exemption |



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4.2. | Providing transportation services by small aircraft | No income tax exemption | No income tax exemption |
| 4.3. | Liquid waste filtration and disposal service | No income tax exemption | No income tax exemption |
| 4.4. | Telecommunication service | No income tax exemption | No income tax exemption |
| 4.5. | Crypto Currency Mining | No income tax exemption | No income tax exemption |

## አባሪ ሁለት
## ANNEX 2

## የካፒታል እቃዎች ዝርዝር
## Lists of Capital Goods

**የካፒታል እቃዎች ዝርዝር (Lists of Capital Goods) ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ በቀረበው ሌላ ሰነድ ላይ የሚገኘውን ዝርዝር ይመለከታል።**



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

## አባሪ ሦስት
## ANNEX THREE

## ለገቢ ግብር እፎይታ የሚቀርቡ ሰነዶች ዝርዝር
## DOCUMENTS REQUIRED FOR INCOME TAX HOLIDAY

### የገቢ ግብር እፎይታ ለማግኘት የሚቀርቡ ሰነዶች

1) **ለአዲስ ኢንቨስትመንት**

ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከተሰጠበት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ፤

ለ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

ሐ) አመልካቹ የህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የህብረት ስራ ማህበሩ የምዝገባ ሰርትፊኬት፤

መ) የመሬት ካርታ (በኪራይ ከሆነ የኪራይ ውል)

2) **ለማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ኢንቨስትመንት**

ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከተሰጠበት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ፤

ለ) የማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

ሐ) ለማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ፕሮጀክቱ የዋለ መዋለ ንዋይ የሚያሳይ በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርት፤

መ) ከማስፋፊያ መጠናቀቅ በኃላ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያመረተውን ወይም የሰጠውን አገልግሎት መጠን የሚያሳይ በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርት

ሠ) ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ ሆኖ የቆየ ከሆነ ከንግድ ትርፍ ግብር ነፃ ሆኖ በቆየባቸው አመታት ውስጥ የገቢ ማሳወቅ ግዴታውን ሲወጣ የቆየ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፣

3) **ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ወደ ውጭ ለሚልክ ባለሀብት**

ሀ) ኢንዱትሪ ፓርክ ውስጥ የሚገኝ ድርጅት ከሆነ 80 በመቶ ምርቱን ለውጭ ገበያ ያቀረበ ስለመሆኑ የሚያስረዳ የጉምሩክ ዲክላሬሽን



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

ለ) ድርጅቱ ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጭ ከሆነ 60 በመቶ ምርቱን ለውጭ ገበያ ያቀረበ ስለመሆኑ የሚያስረዳ የጉምሩክ ዲክላሬሽን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## DOCUMENTS TO BE SUBMITTED FOR INCOME TAX RELIEF

### 1. For New Investments

An investor applying for income tax relief for a new investment shall submit the following documents:

a) A letter of support from the institution that issued the investment license;
b) A copy of the investment license certificate;
c) If the applicant is a cooperative, a valid cooperative registration certificate;
d) A land map or, if applicable, a lease agreement in cases where land has been acquired through lease.

### 2. For Expansion or Upgrading of Investments

An investor seeking income tax relief for an expansion or upgrading project shall submit:

a) A letter of support from the institution that issued the investment license;
b) A valid investment license certificate for the expansion or upgrading project;
c) An audited financial report indicating the investment expenditure incurred for the expansion or upgrading project;
d) An audited financial report demonstrating the volume of production or services rendered within one year following the completion of the expansion;
e) Where the investor has previously been exempted from business profit tax, documentary evidence confirming compliance with income tax reporting obligations during the exemption period.

### 3. For Investors Engaged in Export Activities

An investor engaged in export of products or services shall submit:

a) For enterprises located within an industrial park, a customs declaration verifying that at least 80% of the products have been exported;
b) For enterprises located outside an industrial park, a customs declaration verifying that at least 60% of the products have been exported.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

## አባሪ አራት
## ANNEX FOUR

## ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ጥያቄዎች ጋር የሚቀርቡ ሰነዶች ዝርዝር
## LIST OF DOCUMENTS REQUIRED FOR CUSTOMS DUTY TAX FREE INCENTIVES

### የቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ጥያቄ ለማስፈቀድ የሚቀርቡ ሠነዶች

1. **ለማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ ለግብርና ዘርፍ፣ የኮንስትራክሽን ስራ ተቋራጭነት፣ ትምህርትና ስልጠና፣ የጤና አገልግሎት፣ የአርኪቴክቸርና የኢንጂነሪንግ ሥራዎች እና ተዛማች የቴክኒክ ማማከር አገልግሎት፣ የቴክኒክ ምርመራና ትንተና፣ የሎጀስቲክስ አገልግሎት፣የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ልማት፣ የኤሌክሪክ ኃይል ማመንጨት ማስተላለፍና ማከፋፈል፣ ቡታ ጋዝ ወይም ቢትመን ማስመጣት እና ነዳጅና የነዳጅ ምርቶችን ማቅረብና የራስን ምርት በጅምላ መሸጥ**

1.1. **የካፒታል ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስፈቀድ፡-**

ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከተሰጠበት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ፤

ለ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

ሐ) አመልካቹ የህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የህብረት ስራ ማህበሩ የምዝገባ ሰርትፊኬት፤

መ) የግዢ ደረሰኝ (Commercial Invoice)፣ የተጫኑት ዕቃዎች ዝርዝር (packing list)፣ የማስጫኛ ሠነድ (Bill of Loading/ Air way Bill/Truckway Bill)፣

ሠ) የመሬት ካርታ (በኪራይ ከሆነ የኪራይ ውል)

1.2. **መለዋወጫ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስፈቀድ፡-**

ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለተሰጠበት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ፤

ለ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

ሐ) የንግድ ሥራ ፈቃድ ሰርተፍኬት (ሥራ ከጀመረ)፣

መ) አመልካቹ የህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የህብረት ስራ ማህበሩ የምዝገባ ሰርትፊኬት፤



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

ሠ) የግዢ ደረሰኝ (Commercial Invoice)፣ የተጫኑት ዕቃዎች ዝርዝር (packing list)፣ የማስጫኛ ሠነድ (Bill of Loading/ Air way Bill/Truckway Bill)፣

ሰ) መለዋወጫው ከካፒታል ዕቃ ዋጋ 15% ያልበለጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ በባለሀብቱ የተሞላ ማቀናነሻ (ትክክለኛነቱ በኢንቨስትመንት ተቋሙ መረጋገጥ አለበት)፣

ረ) የመሬት ካርታ (በኪራይ ከሆነ የኪራይ ውል)

1.3. **የግንባታ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስፈቀድ፡-**

ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለተሰጠበት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ፤

ለ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

ሐ) አመልካቹ የህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የህብረት ስራ ማህበሩ የምዝገባ ሰርትፊኬት፤

መ) የግዢ ደረሰኝ (Commercial Invoice)፣ የተጫኑት ዕቃዎች ዝርዝር (packing list)፣ የማስጫኛ ሠነድ (Bill of Loading/ Air way Bill/Truckway Bill) ቅጂ፣

ሠ) ለግንባታው የሚያስፈልጉትን የግንባታ እቃዎች አይነት እና ብዛት የያዘ፤ የግንባታ ፈቃድ በሚሰጠው ስልጣን ባለው የመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ የተረጋገጠ የተፈላጊ የግንባታ እቃዎች ብዛት ሰነድ (Bill of Quantity)፣

ረ) የግንባታ ግብዓቱ በተፈላጊ ዕቃ ብዛት ሰነድ ላይ የሚገኝ መሆኑን በባለሀብቱ ተሞልቶ የተረጋገጠ ማቀናነሻ (ትክክለኛነቱ በኢንቨስትመንት ተቋሙ መረጋገጥ አለበት)፣

ሰ) ስልጣን ባለው የመንግስት አካል የተረጋገጠ የፀና የግንባታ ፈቃድ፤

ሸ) የመሬት ካርታ፣

## 2. ሆቴል

2.1. **የግንባታ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስፈቀድ፡-**

ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለተሰጠበት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ፤

ለ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

ሐ) አመልካቹ የህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የህብረት ስራ ማህበሩ የምዝገባ ሰርትፊኬት፤

መ) የግዢ ደረሰኝ (Commercial Invoice)፣ የተጫኑት ዕቃዎች ዝርዝር (packing list)፣ የማስጫኛ ሠነድ (Bill of Loading/ Air way Bill/Truckway Bill) ቅጂ፣



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

ሠ) ለግንባታው የሚያስፈልጉትን የግንባታ እቃዎች አይነት እና ብዛት የያዘ፤ የግንባታ ፈቃድ በሚሰጠው ስልጣን ባለው የመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ የተረጋገጠ የተፈላጊ የግንባታ እቃዎች ብዛት ሰነድ (Bill of Quantity /BOQ/)፣

ረ) የግንባታ ግብዓቱ በተፈላጊ ዕቃ ብዛት ሰነድ ላይ የሚገኝ መሆኑን በባለሀብቱ ተሞልቶ የተረጋገጠ ማቀናነሻ (ትክክለኛነቱ በኢንቨስትመንት ተቋሙ መረጋገጥ አለበት)፣

ሰ) ስልጣን ባለው የመንግስት አካል የተረጋገጠ የፀና የግንባታ ፈቃድ፤

ሸ) የመሬት ካርታ፣

ቀ) የቱሪዝም ሚኒስቴር ሆቴሉ ሲጠናቀቅ የሚኖረውን የኮከብ ደረጃ የሚገልፅ ደብዳቤ፣

## 3. የአስጎብኚነት አገልግሎት

### 3.1. የካፒታል ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስፈቀድ፡-

ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከተሰጠበት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ፤

ለ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

ሐ) አመልካቹ የህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የህብረት ስራ ማህበሩ የምዝገባ ሰርትፊኬት፤

መ) የግዢ ደረሰኝ (Commercial Invoice)፣ የተጫኑት ዕቃዎች ዝርዝር (packing list)፣ የማስጫኛ ሠነድ (Bill of Loading/ Air way Bill/Truckway Bill)፣

ሠ) የመሬት ካርታ (በኪራይ ከሆነ የኪራይ ውል)

ረ) የአስጎብኚነት አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ፤

### 3.2. የግንባታ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስፈቀድ፡-

ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለተሰጠበት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ፤

ለ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

ሐ) አመልካቹ የህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የህብረት ስራ ማህበሩ የምዝገባ ሰርትፊኬት፤

መ) የግዢ ደረሰኝ (Commercial Invoice)፣ የተጫኑት ዕቃዎች ዝርዝር (packing list)፣ የማስጫኛ ሠነድ (Bill of Loading/ Air way Bill/Truckway Bill) ቅጂ፣

ሠ) ለግንባታው የሚያስፈልጉትን የግንባታ እቃዎች አይነት እና ብዛት የያዘ፤ የግንባታ ፈቃድ በሚሰጠው ስልጣን ባለው የመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ የተረጋገጠ የተፈላጊ የግንባታ እቃዎች ብዛት ሰነድ (Bill of Quantity /BOQ/)፣



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

ረ) የግንባታ ግብዓቱ በተፈላጊ ዕቃ ብዛት ሰነድ ላይ የሚገኝ መሆኑን በባለሀብቱ ተሞልቶ የተረጋገጠ ማቀናነሻ (ትክክለኛነቱ በኢንቨስትመንት ተቋሙ መረጋገጥ አለበት)፣

ሰ) ስልጣን ባለው የመንግስት አካል የተረጋገጠ የፀና የግንባታ ፈቃድ፤

ሸ) የመሬት ካርታ፣

ቀ) የአስጎብኚነት አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ፤

## 4. ተሸከርካሪን የማይጨምር የካፒታል ዕቃዎች ኪራይ

### 4.1. የካፒታል ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስፈቀድ፡-

ሀ) ከሊዝ ፋይናንስ አቅራቢው ድርጅት የድጋፍ ደብዳቤ፤

ለ) ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሰጠ የሊዝ ፋይናንስ ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

ሐ) የሊዝ ፋይናንስ አቅራቢው ድርጅት ንግድ ሥራ ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

መ) የግዢ ደረሰኝ (Commercial Invoice)፣ የተጫኑት ዕቃዎች ዝርዝር (packing list)፣ የማስጫኛ ሠነድ (Bill of Loading/ Air way Bill/Truckway Bill) ቅጂ፣

መ) ግዢው የተፈጸመው ከአገር ውስጥ ከሆነ የሦስትዮሽ የሽያጭ ውል፤

ሠ) የተከራይ ንግድ ሥራ ፈቃድ ሰርተፍኬት፤

## 5. የማዕድን፣ ነዳጅ፣ ጂኦተርማል እና ባዮፌውል ስራዎች

### 5.1. የካፒታል ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስፈቀድ፡-

ሀ) የማዕድን/ነዳጅ/ጂኦተርማል/ባዮፌውል ሥራ ፈቃድ ከተሰጠበት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ፤

ለ) የማዕድን/ነዳጅ/ጂኦተርማል/ባዮፌውል ሥራ ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

ሐ) የንግድ ሥራ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ፣ (ካለ)

መ) አመልካቹ የህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የህብረት ስራ ማህበሩ የምዝገባ ሰርትፊኬት፤

ሠ) የግዢ ደረሰኝ (Commercial Invoice)፣ የተጫኑት ዕቃዎች ዝርዝር (packing list)፣ የማስጫኛ ሠነድ (Bill of Loading/ Air way Bill/Truckway Bill)፣

ረ) የመሬት ካርታ፤

ሸ) የማዕድን/ነዳጅ/ጂኦተርማል/ ስምምነት፤



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

5.2. መለዋወጫ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስፈቀድ፡-

ሀ) የማዕድን/ነዳጅ/ጂኦተርማል/ባዮፊውል ሥራ ፈቃድ ከተሰጠበት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ፤

ለ) የማዕድን/ነዳጅ/ጂኦተርማል/ባዮፊውል ሥራ ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

ሐ) የንግድ ሥራ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ፣ (ካለ)

መ) አመልካቹ የህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የህብረት ስራ ማህበሩ የምዝገባ ሰርትፊኬት፤

ሠ) የግዢ ደረሰኝ (Commercial Invoice)፣ የተጫኑት ዕቃዎች ዝርዝር (packing list)፣ የማስጫኛ ሠነድ (Bill of Loading/ Air way Bill/Truckway Bill)፣

ረ) የመሬት ካርታ፤

ሸ) የማዕድን/ነዳጅ/ጂኦተርማል/ ስምምነት፤

ሰ) መለዋወጫው ከካፒታል ዕቃ ዋጋ 15% ያልበለጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ በባለሀብቱ የተሞላ ማቀናነሻ (ትክክለኛነቱ በማዕድን/ በነዳጅ/ በጂኦተርማል/ በባዮፊውል ተቋሙ መረጋገጥ አለበት)፣

ረ) የማዕድን/ነዳጅ/ጂኦተርማል/ ስምምነት፤

5.3. የግንባታ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ለማስፈቀድ፡-

ሀ) የማዕድን/ነዳጅ/ጂኦተርማል/ባዮፊውል ሥራ ፈቃድ ከተሰጠበት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ፤

ለ) የማዕድን/ነዳጅ/ጂኦተርማል/ባዮፊውል ሥራ ፈቃድ ሰርተፍኬት፣

ሐ) አመልካቹ የህብረት ስራ ማህበር ከሆነ የህብረት ስራ ማህበሩ የምዝገባ ሰርትፊኬት፤

መ) የግዢ ደረሰኝ (Commercial Invoice)፣ የተጫኑት ዕቃዎች ዝርዝር (packing list)፣ የማስጫኛ ሠነድ (Bill of Loading/ Air way Bill/Truckway Bill) ቅጂ፣

ሠ) ለግንባታው የሚያስፈልጉትን የግንባታ እቃዎች አይነት እና ብዛት የያዘ፤ የግንባታ ፈቃድ በሚሰጠው ስልጣን ባለው የመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ የተረጋገጠ የተፈላጊ የግንባታ እቃዎች ብዛት ሰነድ (Bill of Quantity)፣

ረ) የግንባታ ግብዓቱ በተፈላጊ ዕቃ ብዛት ሰነድ ላይ የሚገኝ መሆኑን በባለሀብቱ ተሞልቶ የተረጋገጠ ማቀናነሻ (ትክክለኛነቱ በኢንቨስትመንት ተቋሙ መረጋገጥ አለበት)፣

ሰ) ስልጣን ባለው የመንግስት አካል የተረጋገጠ የፀና የግንባታ ፈቃድ፤



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

ሸ) የመሬት ካርታ፣

ቀ) የማዕድን/ነዳጅ/ጂኦተርማል/ ስምምነት፤

**Documents to Be Submitted for Approval of Customs Duty Tax Incentive Requests**

1. **This provision applies to investors engaged in the manufacturing industry, agriculture, construction contracting, education and training, health services, architectural and engineering works and related technical consultancy services, technical inspection and analysis, logistics services, information and communication technology development, electric power generation, transmission and distribution, import of butane or bitumen, the supply of fuel and oil products, and the wholesale of their own products.**

**1.1. For the Approval of Capital Goods Exempt from Taxes and Duties**

An investor seeking approval for the importation of capital goods free from tax and customs duties shall submit the following documents:

a. A letter of support from the institution that issued the investment license;
b. A valid investment license certificate;
c. Where applicable, the cooperative registration certificate;
d. Commercial invoice, packing list, and bill of lading/airway bill/truckway bill;
e. A land map or lease agreement, if the land is leased.

**1.2. For the Approval of Spare Parts and Accessories to Be Imported Duty-Free**

An investor applying to import spare parts and accessories exempt from taxes and customs duties shall submit:

a. A letter of support from the institution that issued the investment license;
b. A valid investment license certificate;
c. A valid business license certificate (if operational);
d. Where applicable, a cooperative registration certificate;
e. Commercial invoice, packing list, and bill of lading/airway bill/truckway bill;
f. A declaration completed and signed by the investor affirming that the value of the spare parts and accessories does not exceed 15% of the value of the associated capital goods (to be verified by the relevant investment institution);
g. A land map or lease agreement, if applicable.

**1.3. For the Approval of Construction Materials to Be Imported Duty-Free**

An investor requesting approval to import construction materials exempt from customs duties and taxes shall submit:



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

a. A letter of support from the institution that issued the investment license;
b. A valid investment license certificate;
c. Where applicable, the cooperative registration certificate;
d. Commercial invoice, packing list, and bill of lading/airway bill/truckway bill;
e. A list specifying the types and quantities of construction materials required for the project, accompanied by a Bill of Quantities (BQ) certified by the head of the authorized government body responsible for issuing construction permits;
f. A statement completed and certified by the investor affirming that the requested construction materials are included in the certified BQ (subject to verification by the relevant investment institution);
g. A valid construction permit issued and certified by the competent government body;
h. A land map or, if applicable, a lease agreement.

## 2. Hotel Sector

### 2.1. For Exemption of Construction Materials from Duties and Taxes

To apply for the importation of construction materials exempt from customs duties and taxes, hotel investors must submit the following documents:

a. Letter of support from the institution that issued the investment license;
b. Valid investment license certificate;
c. If applicable, registration certificate of the cooperative;
d. Commercial invoice, packing list, and a copy of the bill of lading/airway bill/truckway bill;
e. Bill of Quantities (BOQ) specifying the type and quantity of construction materials required, certified by the head of the authorized government body responsible for issuing the construction license;
f. Statement prepared and certified by the investor confirming that the construction materials are included in the BOQ (subject to verification by the investment institution);
g. Valid construction license issued and certified by the authorized government body;
h. Land map or lease agreement (if applicable);
i. Letter from the Ministry of Tourism confirming the total area of the hotel upon completion.

## 3. Tour Guide Service Sector

### 3.1. For Exemption of Capital Goods from Duties and Taxes



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

Tour guide service providers applying for tax exemption on capital goods must submit:

a. Letter of support from the institution that issued the investment license;
b. Valid investment license certificate;
c. If applicable, registration certificate of the cooperative;
d. Commercial invoice, packing list, and bill of lading/airway bill/truckway bill;
e. Land map or lease agreement (if applicable);
f. Tour guide service qualification certificate.

### 3.2. For Exemption of Construction Materials from Duties and Taxes

To qualify for tax exemption on construction materials, tour guide service providers must submit:

a. Letter of support from the institution that issued the investment license;
b. Valid investment license certificate;
c. If applicable, registration certificate of the cooperative;
d. Commercial invoice, packing list, and bill of lading/airway bill/truckway bill;
e. Bill of Quantities (BOQ) specifying the type and quantity of construction materials, certified by the head of the authorized government body responsible for issuing the construction license;
i. Statement confirming the inclusion of the construction materials in the BOQ, prepared and certified by the investor (the relevant investment institution);
f. Valid construction permit certified by the authorized government body;
g. Land map or lease agreement (if applicable);
h. Tour guide service qualification certificate.

## 4. Leasing of Capital Goods (Excluding Vehicles)

### 4.1. For Tax Exemption on Capital Goods

Leasing companies seeking tax exemption on capital goods (excluding vehicles) must submit the following:

a. Letter of support from the leasing finance provider;
b. Lease finance license certificate issued by the National Bank of Ethiopia;
c. Business license certificate of the leasing finance provider;
d. Commercial invoice, packing list, and bill of lading/airway bill/truckway bill;
e. Tripartite sales contract if the purchase is made locally;
f. Business license certificate of the lessee.

## 5. Mining, Petroleum, Geothermal, and Biofuel Operations



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

### 5.1. For Exemption of Capital Goods from Duties and Taxes

Applicants engaged in mining, petroleum, geothermal, or biofuel operations must submit the following documents to qualify for tax and duty exemption on capital goods:

a. Letter of support from the institution that issued the operation license;
b. Valid operation license certificate (mining, petroleum, geothermal, or biofuel);
c. Copy of business license (if available);
d. Registration certificate if the applicant is a cooperative;
e. Commercial invoice, packing list, and bill of lading/airway bill/truckway bill;
f. Land map or lease agreement;
g. Mining/ petroleum /geothermal/biofuel concession or operations agreement.

### 5.2. For Exemption of Spare Parts from Duties and Taxes

To qualify for tax and duty exemption on spare parts for eligible operations, the following documents must be submitted:

a. Letter of support from the institution that issued the operation license;
b. Valid operation license certificate (mining, petroleum, geothermal, or biofuel);
c. Copy of business license (if available);
d. Registration certificate if the applicant is a cooperative;
e. Commercial invoice, packing list, and bill of lading/airway bill/truckway bill;
f. Land map or lease agreement;
g. Mining/petroleum/geothermal/biofuel concession or operations agreement;
h. A signed statement by the investor confirming that the cost of the spare parts does not exceed 15% of the value of the capital goods, with accuracy verified by the appropriate licensing institution.

### 5.3. For Exemption of Construction Materials from Duties and Taxes

Applicants seeking construction material tax and duty exemption must submit:

a. Letter of support from the institution that issued the operation license;
b. Valid operation license certificate (mining, petroleum, geothermal, or biofuel);
c. Registration certificate if the applicant is a cooperative;
d. Commercial invoice, packing list, and bill of lading/airway bill/truckway bill;
e. Bill of Quantities (BOQ) detailing the types and quantities of construction materials, certified by the competent government authority issuing the construction permit;



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025

f. Investor's statement confirming the materials listed in the BOQ, verified by the investment institution;
g. Valid construction permit certified by the competent authority;
h. Land map or lease agreement;
i. Mining/ petroleum/geothermal/biofuel concession or operations agreement.



Uploaded on the Website of the Ministry of Finance on May 29, 2025